# በአኹኑ ሰዓት ፡ በሊብያ አገር ፡ በእስላሞች ሠይፍ ስለታረዱት ኢትዮጵያውያን ፡ ተጠያቂው ማን ነው? መፍትሔውስ ምንድር ነው?

ይህንኑ አስመልክቶ፡ ከደቡብ አፍሪቃው የግፍ ዕልቂት በኋላ፥ አኹንም ድረስ፡ በኢትዮጵያውያትና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የ"እግዚኦታ" እና "ፈኑ እዴከ እምአርያም!"፡ ማለትም፡ "እጅህን ከአርያም ላክ!"[፩] የሚሉ፡ አሳፋሪና ዓመፀኛ ጸሎቶችና ልመናዎች፥ ምልጃዎችና ምሕላዎች እንደቀጠሉ ይገኛሉ።

ነገር ግን፡ ይህ እየኾነ ያለው፡ የነቢዩ የልመና መዝሙር፡ ዘለዓለማዊውን ምላሽ አግኝቶ፡ በኪዳነምረቱ፡ የውዳሴ ማርያም ምስጋናችን እንኳ፡ "ተፈሥሒ! ወተሐሠይ! ኦ ዘመደ ዕጓለ እምሕያው፤ እስመ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም፤ ወመጠወ፡ ወልዶ ዋሕደ፡ ከመ ይሕየው ኵሉ ዘየአምን ቦቱ እስከ ለዓለም፤ ፈነወ ለነ መዝራእቶ ልዑል። ንዌድሰኪ፡ ኦ ቅድስት! እስመ በትንባሌኪ ዘእም፡ ረከብነ ሣህለ ወልድኪ ዘለዓለም።"

ማለትም፡ "የሰው ወገን የኾንህ ፍጡር ኹሉ፡ እጅግ ደስ ይበልህ! ሐሤትም አድርግ! እግዚአብሔር አብ፡ ዓለሙን ወድዶታልና፤ በእርሱ የሚያምን ኹሉ፡ ለዘለዓለም ይድን፥ ሕያውም ኾኖ ይኖር ዘንድ፡ አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በቤዛነት አሳልፎ ሰጥቶለታል፤ እግዚአብሔር አብ፡ እንዲህ አድርጎ፡ <u>ኃያል ክንዱን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ሰደደልን።</u> ቅድስት ሆይ! የእናትነት ምልጃሽ፡ የልጅሽን ዘለዓለማዊ ይቅርታ ስላስገኘልን፡ እናወድስሻለን።"[፪] በማለት፡ የምናመሰግን መኾኑ እየታወቀ ነው።

በመኾኑም፡ ከዓመታት በፊት፡ "ፈደዩኒ እኪተ፡ ህየንተ ሠናይት"፡ ማለትም "ስለበጎ፡ ክፋትን መለሱልኝ"[፫] በሚል ርእስ፡ በሳውዲ የዓረብ አገር፥ ከጥቂት ቀናት በፊትም፡ በደቡብ አፍሪቃ አገር በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ላይ የተፈጸመውን ግፍ አስመልክቶ ያወጣነውን ጽሑፍ፥ አኹንም ለተፈጠረው አሠቃቂ ክሥተት፥ ወደፊትም፡ ይህ ትውልድ፡ ወደመለኮታዊው የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱና ምግባሩ፡ እራሱን፡ በእውነተኛ ንስሓ አስተካክሎ እስካልተመለሰ ድረስ ለሚቀጥለው ግፍና ሰቆቃ፡ ይህው፡ መፍረጃ እንዲኾን ቀርቧልና፡ ይኸውላችሁ፡ በአትኵሮት ተመልከቱት!



ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፡ ኢትዮጵያውያንም፤ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን፡ ለማስረዳት፡
የ ‘‘ኢትዮጵያ’’ እና የ ‘‘ኢትዮጵያውያን’’ የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ።
ለተጨማሪ እውነት ጎዋ ሰሌዳችንን ይጎብኙ። http://www.ethiopiathekingdomofgod.org

To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;
and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians
For further details on the “Truth” visit our website: http://www.ethiopiathekingdomofgod.org

መቼም፡ የጉድለቱና የስሕተቱ፥ የጥፋቱና የችግሩ አመንጭዎች ብቻ ሳይኾኑ፡ ይኸው፡ ሰለባዎችም ጭምር እስከመኾን የደረሱት፡ እየራሳቸው፡ ወገኖቻችን የኾኑት፡ ሰብአውያን ፍጡሮች እንጂ፡ ከቸሩ ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር እና ከቅድስት እናቱ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፡ ሳይደረግልን የቀረ፡ አንዳችም ጸጋና በረከት እንደሌለ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት እንደተገነዘብነው እናምናለን።

እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ በዚህ ረገድ፡ በእኛ በኩል፡ የሱባኤና የምሕላ ጸሎታችንን (ምስጋናችንን)፡ ለአርባ ዓመታት፡ ለአንዷት አፍታ እንኳ ሳናስታጕል፡ እስካኹን እንደቀጠልን ኹሉ፡ አኹንና ወደፊትም፡ ይህንኑ ትጋሃችንን እንደምንቀጥል፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት ዘንድ የታወቀ ነው።

ታዲያ! የመከራው ጽዋ ተቀባዮች ኹሉ፥ መሰሎቻቸው ጭምር፡ አኹንና ከዚህ በኋላ፡ ምን ለማድረግ እያሰቡ ነው? ካለፈው አደገኛና ከባድ የክህደትና የዓመፅ ጥፋታቸው፡ በእውነተኛ ንስሓ እየተጸጸቱ፡ ወደእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸውና ማንነታቸው እየራሳቸውን ሊመልሱ ወስነዋልን? ቈርጠዋልን? ተዘጋጅተዋልን?

እንግዴህ፡ ልናይ፥ ምስክሮችም ልንኾን ነው።

## <u>*የጥቅስ ዝርዝር ፡—*</u>

*፩፡ (መዝ. ምዕ. ፩፻፵፫፥ ቍ. ፯፤ ከግእዙ የቅዱስ መጽሐፍ አብነት።)*
*፪፡(የሰኞ ውዳሴ ማርያም፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ ሦስተኛ መጽሐፍ፤ በንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፤ ገጽ ፵፯።)*
*፫፡(መዝ. ምዕ. ፷፰፥ ቍ. ፴፩፤ ከግእዙ የቅዱስ መጽሐፍ አብነት።)*